# ሰማያዊ ፓርቲ ለሰማያዊ ህይወት ወይስ ለፖለቲካ...

ኑርዘላለም ታከለ

ትግራይ ኦንላይን April 19, 2014

ሰማያዊ ፓርቲ በነደፈው የነውጥ ሥልት በአገር ውስጥና በውጭ ሚዲያዎች ስሙ ተደጋግሞ ከመነሳቱ ውጭ የፈጠረው አዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብም ይሁን የተረጋጋ ፖለቲካ እንዲኖር ያደረገው አንድም እንቅስቃሴ የለም። ሰማያዊ ፓርቲ እሱን መሰል ፓርቲዎች ከዚህ በፊት ይሞክሩት የነበረውን መንገድ በመከተል የበሬ ወለደ አካሄድን ሲመርጥ ተመልክተናል።

የመጀመሪያው ነገር ሰማያዊ ፓርቲ ከአቅሙ በላይ በመንጠራራት የተቃዋሚ ፓርቲ መሆን ከእኔ በላይ ዓይነት አካሄድ መከተሉ የትም የሚያደርሰው አይደለም። የሰማያዊ ፓርቲ መሪ ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት በቅርቡ በሰጡት ቃለምልልስ ለአገራችን ተቃዋሚዎች ሰላማዊ ሰልፍ ያሳየናቸው እኛ ነን ብለዋል፤ የሚገርም አባባል ነው።

ሰላማዊ ሰልፍ እሳቸው እንደሚሉት ሰማያዊ ፓርቲ ለዜጎች የፈቀደ ሳይሆን ህገ -መንግስቱ ያረጋገጠው ዴሞክራሲያዊ መብት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህም ሆኖ ግን ሰላማዊ ሰልፍ የሚደረግበት ጉዳይ ሳይኖር ለረባውም ሆነ ላልረባው ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት የማያስፈልግ መሆኑን ኢንጂነሩ ዘንግተውታል መሰለኝ።

ሰማያዊ ፓርቲ መሪ ሊነግሩን የሚፈልጉት በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተወዳድረው ስልጣን ከመያዝ ይልቅ በአቋራጭ በቀለም አብዮት አራማጆች ስልጣን ላይ መፈናጠጥን ነው።

ኢንጂነሩ በቅርቡ አውሮፓና አሜሪካ ደርሰው ከተመለሱ በኋላ በአሜሪካ ቆይታቸው የዴሞክራሲ ተቋማት ከሚሏቸው ነገር ግን በተግባር የቀለም አብዮት አራማጆች ጋር ውይይት እንዳደረጉ በይፋ ሲነግሩን ነበር።

ሰማያዊ ፓርቲ  ተቋቁሞ ገና በሁለት እግሩ  መቆም ሳይችል በህገ መንግስቱ ላይ  በግልጽ የተደነገገውን ቀዩን መስመር በመተላለፍ ሃይማኖትንና ፖለቲካን  ማተረማመስ አባዜ ውስጥ በመዘፈቅ የአክራሪዎች ጥያቄ የፓርቲዬ ዓላማ ነው ሲሉ በግልጽ ተናግረዋል፡፡

የፓርቲው ሊቀመንበር በቅርቡ ከኢትዮ-ምህዳር ጋዜጣ ጋር ባካሄዱት ቃለ ምልልስ ላይ እንዳሉት "መንግስትና ሀይማኖት አይገናኙም ማለት ፖለቲካና ሀይማኖት አይገናኙም ማለት አይደለም፣  ለእምነት ነጻነት መታገል የፖለቲካ ጥያቄ ነው" ኢንጂነሩ በአገራችን የሃይማኖት ነፃነት እንዳልተከበረ አድርገው መንግስታዊ ሃይማኖት ወይም ሃይማኖታዊ መንግስት እንዳለ በማስመሰል ለእምነት ነጻነት ትግል ማቅረብ አግባብ አይመስለኝም።

ከአክራሪዎች ጋር በሚደረግ ቁርኝት የሚገኝ የፖለቲካ ትርፍ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እጅግ የከፋ መዘዙ ለቀጣይ ትውልድ እንደሚተርፍ ኢንጂነሩ አልተረዱም። ለዚህም ነው  ሰማያዊ ፓርቲ ገና ከመፈጠሩ ከአግባብ ውጭ ትርፍ ያስገኝልኛል ብሎ ያሰበውን ሃይማኖትን ከለላ በማድረግ እውቅና ማግኘትን የፈለገው።

በተመሳሳይ የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ኢንጂነር ይልቃል በዚያው ሰሞን ለሪፖርተር ጋዜጣ እንደገለጹት «ፖለቲካና ሃይማኖት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው፤ በመሆኑም አይገናኙም ብሎ ነገር የለም፤» ብለዋል።

እንደ እኔ ግን ሃይማኖትና ፖለቲካ ለየቅል በመሆናቸውም ይመስለኛል በህገ መንግስታችን ላይ መንግስት በሃይማኖት፣ ሃይማኖትም በመንግስት አሰራር ጣልቃ እንዳይገባቡ ግልፅ መስመር የተቀመጠው።

ኢንጂነር የእርስዎ ሰማያዊ ፓርቲ ስልጣን ቢይዝ ይህን መስመር ሊያጠፉትና መንግስታዊ እምነት ወይም ሃይማኖታዊ መንግስት ያቋቁሙልን ይሆን? ስል ሁሌም አስባለሁ። የፖለቲካ ፓርቲዎች የመጨረሻ ግብ ሥልጣን በመቆጣጠር መንግስት መመስረት እንጂ እንደ ሃይማኖት ለጽድቅ የሚሰራ አይመስለኝም።

ታዲያ ኢንጂነር ይልቃል ነገር አሳመርኩ ደጋፊ አገኛለሁ በማለት ፖለቲካና ሃይማኖት የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው በማለት የሚደሰኩሩት የአክራሪነትን ረመጥ ያወቁት አይመስለኝም።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የአንድ የሃይማኖት አማኞችን ጥያቄ እንደ አጀንዳ አድርገው ሲንቀሳቀሱ በመንግሥት ላይ ተፅዕኖ ከመፍጠር አልፎ፣ የመንግሥት ለውጥ ለማድረግ ጥቅም ላይ ከዋለ ገመዱ ተበጠሰ ማለት ነው ይላሉ፡፡

መንግስት በእውነት የእምነት ነጻነትን የሚጋፋ ተግባር ፈጽሞ ከሆነ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለዜጎች ሃይማኖታዊ መብት መከበር መከራከር የለባቸውም ማለቴ ሳይሆን በአገራችን ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ የሃይማኖት ነጻነት በአገሪቱ ህገመንግስት የተረጋገጠበት ሁኔታ አለ፤

አንዳንድ ድብቅ አጀንዳ ያላቸው ግለሰቦች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሃይማኖትን ሽፋን አድርገው በግልጽ እየተንቀሳቀሱ እንደሆነም ይታወቃል፡፡ ሰማያዊ ፓርቲም ይህን ጉዳይ የፖለቲካ መጠቀሚያ ለማድረግ መሯሯጡ ረጅም መንገድ የሚያስኬደው አይመስለኝም።

ይህን ስል የኢንጂነሩ ፓርቲ የእምነት ነፃነታቸው በእውኑ ተጥሶ ከሆነ መቃወም የለባቸውም ማለቴ ሳይሆን፣ እንዲህ ያለ ሁኔታ በሌለበት ሃይማኖትን አጀንዳ አድርገው መንቀሳቀሳቸው ፓርቲያቸው በሃይማኖት ተፅዕኖ ስር የወደቀ ሴኪዩላሪዝምን የማያራምድ መሆኑን ያሳያል።

በአገራችን እንዲህ ያለ የሃይማኖት አብዘሃነት ባለበት ሁኔታ ሃይማኖታዊ መንግስት መናፈቅ እውነትም ሰማያዊ ፓርቲ ለሰማያዊ ህይወት እንጂ ሴኪዩላር እንዳልሆነ ያሳያል። ኢንጂነሩም የሃይማኖት ጉዳይን በማንሳት በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ እውቅና አገኛለሁ ብለው አስበዋል፡ ሆኖም ሙስሊሙ ማህበረሰብ ቀድሞ የአክራሪዎችን አካሄድ ያወቀ በመሆኑ ሙከራዎቹ ሁሉ እንደማይሳኩ ሊረዱ ይገባል፡፡

ምክንያቱም እነዚህ የአክራሪ ሙስሊሞችን ጥያቄ የሚያናፍሱ ፓርቲዎች በምርጫ በለስ ቢቀናቸው ምን ዓይነት መንግሥት እንደሚያቋቁሙ መገመትም ከባድ አይሆንም፡፡

በአገራችን በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ አንዳንድ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች በምርጫ የህዝብን ቀልብ መሳብ ሲሳናቸው ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ በማይገባ መንገድ ወደቋመጡላት የስልጣን ማማ የሚያደርሳቸው እየመሰላቸው የሃይማኖት ጉዳይን ከፖለቲካ ጋር ሲደበላልቁት ይታያሉ።

የእነዚህ ፓርቲ አመራሮች "የአክራሪዎችን ድርጊት አይዟችሁ ትግላችሁ አግባብ ነው፣ እንረዳዳ በርቱ ተጠናከሩ" በማለት በየሚዲያው በሚሰጧቸው መግለጫዎችና ቃለ ምልልሶች የአክራሪዎችን አካሄድ ሲያወድሱ እንደነበርም የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡

በተለይ ሰማያዊና አንድነት ፓርቲዎች የሃይማኖትን ነገር ሞታችን ብለው የአክራሪዎችን ህገ ወጥ እንቅስቃሴ ተቀባይነት እንዳለው በማድረግ የተለያዩ ድጋፎችን ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡

ፈረንጆች የማይገባን ጥቅም ከማይገባ ቦታና ጊዜ የሚፈልጉ ሰዎችን ሲገልጿቸው "a fish in troubled water" ይሏቸዋል። እነዚህ ሰዎች ለመናኛ ትርፍ ብለው እንዲህ ያለ አገርንና ወገን የሚጎዳ ነገር ውስጥ መዘፈቃቸው የስልጣን ጥማቸው ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

የእነዚህ ፓርቲዎችና የአክራሪዎች ፍቅር ዘላቂነት እንደማይኖረው ሁለቱም ጠፍቷቸው ሳይሆን እንዲያው ቢጨንቃቸው ጋብቻ ፈጸሙ እንጂ። የእነዚህ ፓርቲ አመራሮች በእንዲህ ያለ ቆሻሻ መንገድ የቋመጡለትን ስልጣን ቢያገኙት እንኳን ስልጣናቸውን ሳያጣጥሙት በአሸባሪዎች ጎርፍ ተጠራርገው እንደሚጠፉ የተገነዘቡት አይመስሉም።

"የጠላቴ ጠላት..." በሚለው የተሳሳተ ብሂል አገርንና ህዝብን ሊጎዳ የሚችል ድርጊት ውስጥ መዘፈቅ ተገቢ አካሄድ አይመስለኝም። "በሬ ሆይ ሳሩን አይተህ ገደሉን ... " እንደሚባለው መሆንም ይመጣልና መጠንቀቅ ተገቢ ይመስለኛል። ምዕራባዊያን የአለማችን ቁጥር አንድ ስጋት የሆነውን አሸባሪነት ከምንጩ ለማድረቅ ሲሉ አህጉራትን አቆራርጠው በመዝመት ላይ ይገኛሉ።

አሜሪካኖችና አውሮፓዎች አስር ሺህ ኪሎ ሜትሮችን አቆራርጠው፤ መቶ ሺህ ወታደሮቻቸውን አሰልፈው፤ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር በመከስከስ አሸባሪዎችን የሚዋጉት ተፈፀመብን ወይም ሊፈፀምብን ይችላል ያሉትን አደጋ ከሩቁ ለመከላከል እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡

ምስራቅ አፍሪካ በተለይ በቀንዱ አካባቢ ለሁለት አስርት አመታት መንግስት አልባ የሆነችው ሶማሊያ የአክራሪዎች ምቹ ስፍራ ሆና መቆየቷ ሽብርተኝነት ለአገራችን ድርስ ስጋት እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳበረከተች የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው።

እንግዲህ አክራሪነት ለአገራችንም ሆነ ለአካባቢው ስጋት እንደሆነ እየታወቀ አንዳንድ የአገራችን የፓርቲ አመራሮች ከአክራሪዎች ጋር እንዲህ ያለ መጓተት ውስጥ መግባታቸው መልካም አካሄድ አይመስለኝም፡፡

ሌላው በአገራችን ያለውን የአክራሪዎች እንቅስቃሴ በማነፍነፍ አይዟችሁ በርቱ ተበራቱ ይሉ የነበሩት አንዳንድ የአገር ውስጥ የህትመት ሚዲያዎችና ከውጭ የሚተላለፉ እንደ አሜሪካና ጀርመን ራዲዮ ጣቢያዎች የመሰሉት ናቸው፡፡

እነዚህ ሚዲያዎች የአሸባሪዎች ድምፅ በመሆን የአክራሪዎች መረጃ መለዋወጫ፣ መጠራሪያና እርስ በርስ መወዳደሻ መሳሪያዎች በመሆን ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡ ዛሬም እነዚህ ሚዲያዎች እንዲህ ያለ አገርንና ህዝብን ለአደጋ ሊያጋልጥ የሚችል ስራ ከመከወን አልተቆጠቡም።

የእነዚህ ሚዲያ ዘገባዎች የበሬ ወለደ ተረት፣ ከእውነት የራቁ አሊያም መናኛ ነገሮችን እጅግ በብዙ ቀለማት በማስጌጥ ስለሚያቀርቡ አንዳንድ የእምነቱ ተከታዮችን የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ስለሚያደርጓቸው ለአክራሪዎች መጠቀሚያ እንዲሆኑ ይዳርጓቸዋል።

በኢትዮጵያ የግጭትና የለውጥ ታሪክ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ በአገራችን ስላለው ሁኔታ ለሪፖርተር ጋዜጣ እንዳሉት በአገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች መብዛት ዋነኛው ምክንያት የግለሰቦች

የሥልጣን ጥመኝነት፣ ሥልጣን ላይ የመቆናጠጥ ፍላጎት፣ እንዲሁም ከሥልጣን ጋር አብረው የሚመጡ ጥቅማ ጥቅሞችን ለመጨበጥ ነው፡፡

በአገራችን የምናያቸው ፓርቲዎች በእምነትና በዲስፕሊን ዙሪያ የተዋቀሩ ፓርቲዎች ባለመሆናቸው ምክንያት ቅንጅት ብቅ ብሎ ለመጥፋቱ አንዱ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

በእርግጥ ሰላማዊ ሰልፍ በአንዲት ዴሞክራሲያዊት ነኝ በምትልና ህዝቦች አምነውና ፈቅደው በወኪሎቻቸው አማካይነት ባፀደቁትና "የሉዓላዊነት መገለጫችን ነው" በሚሉት ህገ መንግስት በምትመራ ሀገር አንዱና የሀገሪቱ ዴሞክራሲያዊነት መገለጫ መሆኑና ለየትኛውም ወገን የማይከለከል መብትና የመታገያ መንገድ መሆኑ ይታወቃል።

ችግሩና ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነኝ ግን ይህንኑ ህገ መንግስታዊ መብት ተጠቅመው ይበጀናል ባሉትና ከአማራጭ ፖሊሲና ፕሮግራም ይልቅ በቅድሚያ ሰላማዊ ሰልፍን የመረጡት ሃይሎች በ"ተከለከልን እና ተቀፈደድን" ጭንብል መንግስትን እና ገዥ ስርዓቱን በማሳጣት የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት የሚሹ ሃይሎች መኖራቸው ነው፡፡ እነዚህም ሃይሎች በርግጥም የከሰሩ ፖለቲከኞች የመሆናቸው ጥግ የታየበት ሰሞንኛው *የአንቺው ታመጪው አንቺው ታሮጪው ፖለቲካ* ነው።

ይህን ለማብራራትና በርግጥም የሀገሬ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስለመክሰራቸውና የክስረታቸውን ጥግ የሚያሳዩ ሰሞንኛ ዘገባዎችን በቅድሚያ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል።

ከሰሞኑ *የሰማያዊ እና አንድነት* ፓርቲ አባልነት እኛም አለንበት የሚሉት *33 ነን* ቢሉም ቀደም ሲል እንደተመለከትነው *አሰራዎቹ* ከሰልፉ በስተጀርባ ለማትረፍ የሞከሩበት ድራማ የሚጀምረው ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር በተያያዘ ሲያስተጋቡት የነበረው አሉባልታ ነው።

ለዚህም ለተለያዩ የሀገር ውስጥ ጋዜጦችና መፅሄቶች *ከቅርብ ወራት ወዲህ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የአደባባይ የተቃውሞ ሰልፍ መጥራት መጀመራቸውን ተከትሎ በኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 30 መሰረት የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት እና አቤቱታ የማቅረብ መብትን ሊገድብ ይችላል የተባለ አዲስ መመሪያ የከተማው አስተዳደር አወጣ* በማለት ቃላቸውን መስጠታቸው ነው።

የሆነው ሆኖ ኢንጂነሩ በመጪው 2007 ምርጫ እወዳደራለሁ ይበሉ እንጂ አላማቸው ሌላ እንደሆነ ማየት ይቻላል። እዚህ ላይ እንዲታወቅ የምፈልገው አሜሪካ ሄደው በኢትዮጵያ የተጀመረው የዴሞክራሲ ስርዓት እንዴት ሊያብብ እንደሚችል ልምድ ለመቅሰም ወይም የእውቀት ሽግግር ለማድረግ አይደለም።

ይልቁንም ኢንጂነሩ ቀደምት ሸሪኮቻቸው አልሳካ ያላቸውን አቋራጭ የስልጣን መሰላል መስቀያዋን መንገድ ለማፈላለግ ነበር። ይህ እጅግ መሰሪ የሆነ ተግባር በአገራችን የተጀመረውን የዴሞክራሲ ስርዓት ከማቀጨጨም በላይ ለራሳቸውም የማይበጃቸው አካሄድ ይመስለኛል።

የቀለም አብዮት አራማጆች ለስልጣን ያበቃናል ብለው ካሰቡ ማንኛውንም ነገር ከመተግበር ወደኋላ እንደማይሉ ከዚህ በፊት ይከተሉት ከነበረው አካሄዳቸው ማየት ይቻላል። ኢንጂነሩ አገርንና ህዝብን ሊያጠፉ የሚችለውን አለም በአንድ አፍ የሚያወግዘውን የአክራሪዎችን ጥያቄዎች በየአደባባዩ አጀንዳችን ነው ሲሉ ተደምጠዋል።

የኢትዮጵያ ህገ መንግስት መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ እንደሆነ በግልፅ ደንግጓል፡ መንግስት ለመሆን ነገ እወዳደራለሁ የሚል ፓርቲ የሃይማኖት መንግስትን ለማቋቋም መፈለጉና የአክራሪ ሃይልን አጀንዳ ማራገቡ የሚያስገርም ነው።

ኢንጂነሩ የሚፈልጉት ይህችን አገር በበጎ ለመለወጥ ሳይሆን በአገራችን የተጀመረው የዴሞክራሲ ስርዓት እንዲወድቅና ይናፍቁት የነበረው የአንድ ፓርቲ አገዛዝ እንዲመሰረት፣ ስልጣን እንደ ድሮው በአንድ ቋት እንዲሰበሰብ ለማድረግ ነው።

አዲስ ተስፋ የተጣለበት ሰማያዊ ፓርቲ የወጣቶች ስብስብ በመሆኑ ሀገሪቱን በማስተዳደር ላይ የሚገኘውን አምባገነን አገዛዝ እድሜ ለማሳጠር ተስፋ የተጣለበት ድርጅት ነው እየተባለም ይለፈፋል፡፡

ለመሆኑ በሚታይና በሚጨበጥ ሁኔታ፣ ቀድሞ ከነበሩት መንግስታትም በላይ ኢትዮጵያ እንዳሁኑ ወቅት ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት እመርታ ያስመዘገበችበት ጊዜ አልነበረም፡፡

ይህንን የተገኘ እድገትና ለውጥ ጠብቀን ሀገሪቱን የበለጠ ለማሳደግ ነው መስራት ያለበት ወይንስ ጭራሹን ለማውደምና ለማጥፋት? ኢሕአዴግን መደገፍ አለመደገፍ የማንኛውም ዜጋ መብት ነው፡፡ ኢሕአዴግን ስለጠሉ የሀገርን ህልውናና ደህንነት አደጋ ውስጥ ለመጣል ከጠላት ጋር መሰለፍና መሳሪያ መሆን ግን ሌላ ጉዳይ ነው፡፡

አሁን ያሉት ተቃዋሚ ኃይሎች አገር የመምራት እድላቸው ከዜሮ በታች ነው፡፡ ይህ የሆነው የሃገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ፖሊሲ የሌላቸው፣ ወደፊት ከማራመድ ይልቅ ድሮ ሞቶ የተቀበረውን ሥርዓት ለመመለስ የሚመኙ በመሆናቸው ነው፡፡

ስለዚህም የእነርሱ አካሄድ የበላይነት ቢያገኝ ሀገሪቱ ወዳልተጠበቀ አቅጣጫ ልታመራም መቻሏ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡

የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ኢንጂነር ይልቃል ጌትነት እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ በኢትዮጵያ ያለው የምርጫ ቦርድ ከስራ አስፈጻሚው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለውና በአንድ ፓርቲ የበላይነት የሚመራና የፓርቲው አንድ ክንፍ በመሆኑ የምርጫ ቦርድ ነፃና ገለልተኛ አይደለም፤ ለቦርዱ የሚሾሙት ግለሰቦች ታሪካቸውንም ከወሰድን በምንም አይነት ገለልተኛነታቸውን የሚያሳይ መረጃ የላቸውም ይላሉ፡፡

ኢንጂነር ይልቃል ምርጫ ቦርዱን ነፃ አይደለም የሚያስብለው ነገር፣ የመንግሥትን መኪናና ንብረቶችንም ሆነ፣ የመንግሥትን ሚዲያ በአግባቡ ይጠቀማል፣ በጀት በአግባቡ ይበጀትለታል፣ የመንግሥት ሰራተኞችም ዕርዳታና ቅስቀሳ እንዲያደርጉ በየጊዜው ነፃ ፈቃድ ይሰጣቸዋል ሲሉም ይናገራሉ፡፡

በዚህም ሳቢያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙ ተቋማት የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የሚሰጡትን መረጃ እንደ ቁም ነገር ሲቆጥሩት አናይም በማለት ከወዲሁ ሂደቱን ለማጣጣል ይሞክራሉ።

ኢህአዴግ ምርጫን የሚጠቀምበት ለማስመሰል ሲሆን ምርጫ ቦርዱም የተቋቋመው ለፈረንጆቹ ስርዓቱ ዴሞክራሲያዊና ገለልተኛ ነው ለማለት ታስቦ እንጂ በተግባር ግን ቦርዱ ነፃ አይደለም በማለት በማስረጃ ሊደገፍ የማይችል ወቀሳ ያቀርባሉ፡፡ መጪው ምርጫ ገና ሳይጀመርም “ተጭበርብሯል” ለማለትም ከወዲሁ ተሰናድተዋል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፤ ከዚሁ ጋር ሌላው የሚገርመው ጉዳይ ፅንፈኛ ተቃዋሚዎች ከወዲሁ አባላቶቼ፣ ደጋፊዎቼ፣ በገዥው ፓርቲ ካድሬዎችና የፀጥታ ሰራተኞች ወከባ ደርሶባቸዋል፣ ተደብድበዋል፣ ታስረዋል፣ ማስጠንቀቂያና ዛቻ ደርሷቸዋል፣ ቤታቸው ተቃጥሏል፣ ተዘርፏል የሚሉ ወሬዎችን በገንዘብ በገዟቸው መፅሄቶች አማካይነት ማሰራጨት ይዘዋል፡፡

ዛሬም እንደ ድሮው በምርጫው ሂደት ሕዝቡ በትክክል ኢሕአዴግን ቢመርጥ “የተጭበረበረ ስለሆነ አንቀበልም” ለማለት ተዘጋጅተዋል፡፡ ጉዳዩን በሰለጠነ መንገድ እንዲጣራ ወደፍርድ ቤት የመውሰድ ፍላጎትም የላቸውም፡፡ በፍርድ ቤቱም እምነት የለንም ባይ ናቸውና፡፡ ይህንንም አስቀድመው ከወዲሁ ማውራትና ማስወራት ጀምረዋል፡፡ “ፍርድ ቤቶች ገለልተኞች አይደሉም” በሚል፡፡

ግንቦት ሰባትና ሌሎች ፅንፈኛ ተቀዋሚዎቸ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሳይሆን በአመጽ መንግስት እንቀይራለን፣ የፖለቲካ ስልጣን እንይዛለን ብለው በወሰኑት መሰረት እነሆ ይህን ለማስፈፀም ተገዝተው ከጎናቸው ተሰልፈዋል፡፡

መሰረታዊ ትኩረታቸው የሀገር ሰላም፣ እድገትና የሕዝብ ተጠቃሚነት አይደለም፡፡ መሰረታዊ ፍላጎታቸውና አላማቸው የሚያውቁትንም፣ የማያውቁትንም፣ ድንገት ጀሯቸው የገባ ጉዳይንም በጥራዝ ነጠቅነት ጨልፈው እየደባለቁ ሕዝብን ውዥንብር ውስጥ መክተት ነው፡፡ ይህን ውዥንብር እየነዙ ለሕገ ወጥ የመንግስት ለውጥ ማነሳሳት ነው፡፡

የዘመናችን የከተማ ሁከት ትሩፋት በግብጽ፣ ሊቢያና ሶሪያ እንደታየው እልቂት፣ የዜጎች መፈናቀልና ስደት የኢኮኖሚ ውድቀት፣ ሥርዓተ አልበኝነት በመጨረሻም ለዓለም አቀፍ አሸባሪዎች የተመቸ መደላድል መሆን ነው፡፡

ከዚህ ያለፈ የሚያስገኘው ፋይዳ የለም፡፡ በአገር ውድመትና በሕዝብ ደም እየነገዱ መክበር የሚፈልጉ የዜግነት ሃላፊነት የማይሰማቸው፤ በጭፍን ጥላቻ ታውረው በቀል የተጠሙ ተቃዋሚዎች ናቸው፡፡

ግንቦት ሰባትን የመሳሰሉ ቡድኖች የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚል እምነት፣ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት የሆነው የኤርትራ መንግስትና ሌሎች የኢትዮጵያን ውድቀት የሚነመጁ አካላት ጉዳይ አስፈፃሚ ቅጥረኛ መሆንን መርጠዋል፡፡ “ቅጥረኛ ሆነው መሰለፍን ለምን መረጡ”? ብሎ ለሚጠይቅ መልሱ ግልጽ ነው፡፡

የኢትዮጵያንና የህዝቧን ፈጣን የኢኮኖሚ ግስጋሴ እድገት መግታት፣ የፀረ ድህነት ትግል አቅሟን ማዳከም በአጠቃላይ ሀገሪቷ የድህነትና የብጥብጥ ማዕከል እንድትሆን የሚፈልጉ በመሆናቸው ነው፡፡ አክራሪ ተቃዋሚዎቹና አሸባሪዎቹ ኢትዮጵያ የጀመረቻቸው ታላላቅ የልማት ፕሮጀክቶች የህዳሴውን ግድብ ጨምሮ ግንባታቸው እንዲስተጓጎልና እንዲቆም እየሰሩ ነው፡፡

የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሕዝብን እምነት የሚሸረሽር ዓይነት ነገር ነው፡፡ የሚገርመው አንድ ሰሞን ኅብረት፣ ውሕደት፣ ቅንጅት፣ ግንባር ምናምን ብለው ተቧድነው እንቅስቃሴ ይጀምሩና ብዙም ሳይቆዩ በቃን ብለው የተናጠል ደፋ ቀናቸውን ይቀጥላሉ።

ይህ ዓይነቱ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አካሄድ መቼም ቢሆን ሲሻሻል አይታይም። ታዲያ በዚህ መልኩ ከቀጠለ የኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ እንዴት ተብሎ ተስፋ ሊጣልበት ይችላል? በሀገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት እንዳያብብ ከሚያደርጉት ዐበይት ምክንያቶች አንዱ የሀገራችን ኤሊቶች የተከፋፈሉ መሆናቸው ነው፡፡

የካቲት 66 አብዮት ዋና ተዋናይ በነበሩት ድርጅቶች መካከል የተጀመረው ክፍፍል አሁንም ድረስ ቂምና ቁርሾ ይዞ እየሰራ ነው፤ በፅንፈኛው ዳያስፖራ እና በአገር ቤት መካከል ያለው ልዩነትና ክፍፍልም ራሱን የቻለ ሌላው የዴሞክራሲ መሰናክል ነው።